# ለሁሉም ነጋዴዎች ትንባሆን ስለማስታወቅ አዲስ የወጣ ሕግ

ከ22 ሴፕቴምበር 2010 ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል

## የትንባሆ ወጤቶችን እና የሲጋራ ማጨሻ ቁሳቁሶችን በግልጥ ማሳየት ተከልክሏል

ከ22 ሴፕቴምበር 2010 ጀምሮ በምእራብ አውስትራሊያ የትንባሆ ውጤቶችን እና የሲጋራ ማጨሻ ቁሳቁሶችን ማሳየት ተከልክሏል።

### የማሳየት መከልከል ምን ማለት ነው?

የትንባሆ ቸርቻሪዎች፤ የትንባሆ ውጤቶችን፤ እያንዳንዱን ፓኮና ካርቶን እንዲሁም የሲጋራ ማጨሻ ቁሳቁሶችን፤ በመሸጫው ሰቅ ውስጥ ከየትኛውም አቅጣጫ እንዳይታዩ ማረጋገጥ አለባቸው።

### በአጋጣሚ መታየት

ከቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት፤ ማለትም ደንበኞች የሚገዟቸውን የሲጋራ ውጤቶች ለማይት በሚጠይቁበት ጊዜ፤ አለያም ሠራተኛው አልፎ አልፎ የመስተካከልና የመደርደር ሥራ በሚያደርጉበት ወቅትና ሽያጩን በሚፈጽሙበት ጊዜ የሚፈጠረውን መታየት አይጨምርም።

ቸርቻሪዎች፤ አልፎ አልፎ የትንባሆ ውጤቶችን በሳጥኖቹ ውስጥ በሚደረድሩበት ጊዜ ከቁጥጥር ውጭ በሆነ ምክንያት ሕዝብ የትንባሆ ውጤቶችንም ሆነ የሲጋራ ማጨሻ ቁሳቁሶችን ሊያዩ ይችሉ ይሆናል።

የጤና ክፍል በእንደዚህ አይነት ከቁጥጥር ውጭ በሆነ፤ አግባብ ባለውና ሃላፊነት ባልጎደለው ምክንያት በንግድ ድርጅቶች ለሚከሰት ልምድ (እንደ መደርደሪያ ማስተካከል ወይም ሕዝብ እያየ በጎደለ መሙላት) መመሪያ አለው። የሁንና፤ ቸርቻሪዎች ያለምክንያት የሳጥኖችን በሮች ወይም ሌሎች ዓይነት መሸፈኛዎችን በጎደለ ከሞሉና ካስተካከሉ በኋላ ክፍት መተው የለባቸውም። የዚህ አይነቱ ስህተት የማስጠንቀቂያ እርምጃ ሊያደርስ ይችላል።

### የዋጋ ትኬቶችና የዋጋ ሰሌዳዎች

እንደወቅቱ ሁኔታ ከሆነ፤ ስለመኖሩ መረጃ ወይም የትንባሆ ውጤቶች ዋጋን በዋጋ ትኬቶችና ሰሌዳዎች ላይ ማሳየት ሊቀጥል ይችላል።

### የማስተማር ዘማቻ

የሚመለከታቸውን የተለያዩ እንዱስትሪዎችን ከማማከር በተጨማሪ፤ የማስተማር ዘመቻም ይካሄዳል። ይህም እንደ በብዙሃን መጋናኛ ስርጭት፤ የሬዮና የጋዜጣ ማስታወቂያዎች፤ በቀጥታ በፖስታ ቤትና በኢሜል ጽሁፎችን ማሰራጨት የመሳሰሉትን የማስተመርና የመረጃ ዘዴዎችን ያካትታል።

### እንዳይታዩ ከታገዱት የማጨሻ ቁሳቁሶች የተከለከሉት የትኞቹ ናቸው?

እንዳይታዩ ከታገዱት የማጨሻ ቁሳቁሶች የሚከተሉት ያካተታሉ፤

- የሲጋራ ወረቀቶች
- የወረቀት ፒፓዎች
- የሲጋራ መያዣዎች
- የመጠቅለያ ምሳሪያዎች
- የትንባሆ ውጤቶችን ለማጨስ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ሁካ እና የውሃ ፒፓዎች
- ትንባሆ ለማጨስ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ቁሳቁሶች በሙሉ።

ክብሪትና የሲጋራ መለኮሻዎች እንደ ማጨሻ ቁሳቁስ አይቆጠሩም፤ ስለሆነም የማሳየት እገዳው አይመለከታቸውምና መታየታቸው መቀጠል ይችላል።

## ሕጉን እንዴት ማስፈጸም ይቻላል?

የምእራብ አውስትራሊያ የጤና ክፍል፤ በተለይም አዳዲስ ሕጋዊ አስፈላጊነት ሲኖር፤ ወቅታዊ ክትትልና ተፈጻሚ ለመሆኑ ቁጥጥር የማድረግ ጠንካራ ትኩረት የሰጣል። ለሕብረተሰቡ ቅሬታ ምላሽ ለመስጠትም ቁጥጥር ያደርጋል።

የጤና ክፍል፤ ደንቡ ተፈጻሚነት እንዲኖረው በርካታና የተለያዩ፤ እንደ ማማከር፤ ማስተማር፤ ሕጋዊ ማስጠንቀቂያ ወይም ክስ የመሳሰሉትን ዘዴዎች ይጠቀማል።

**መገናኛ:**


የትንባሆ ቁጥጥር ቅርንጫፍ
Grace Vaughan House
227 Stubbs Terrace
Shenton Park WA 6008

ስልክ: 1300 784 892
ፋክስ: (08) 9382 0770

የፖስታ አድራሻ:
Department of Health
PO Box 1335
WEST LEEDERVILLE WA 6901

ድረገጽ: www.health.wa.gov.au/tobaccocontrol


### Disclaimer:

The information contained in this factsheet has been produced as a guide only.
To view the full details in the relevant Tobacco Control legislation, visit www.health.wa.gov.au/tobaccocontrol

HP 11901 OCT'10